## <u>አሳሳቢውን የትምህርት ስርዓት ዝቅጠት በኢሮብ ወረዳ ለመቅረፍ ምን መደረግ አለበት?</u>

ክፍል ሶስት፣

### <u>በኢሮብ ወረዳ የትምህርትቤቶች መስፋፋትና የትምህርት ይዘት ዛሬ ምን ይመስላል?</u>

ከበየነ ገብራይ ደንማርክ፣

ከ52 ዓመት በፊት በሞላው የኢሮብ ወረዳ የነበረው አንድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ብቻ ነበር። እሱም ከጣሊያን የኢትዮጵያ ወረራ በኋላ ለብዙ ዓመታት ተዘግቶ ከቆየ በኋላ በ1952 ዓ.ም በክቡር ዶ/ር አባ ወልደማሪያም ካሕሳይ ጥረት በካቶሊክ ቤተክርስትያን ስር ለሁለተኛ ጊዜ የተከፈተው የዓሊተና ልደታ ለማሪያም ት/ቤት ነው። ይህ በክቡር ዶ/ር አባ ወልደማሪያም ካሕሳይ ጥረት በድጋሚ የተከፈተው የልደታ ለማሪያም ት/ቤት ያኔ ሲከፈት ገና ከጅምሩ አዳሪና ተመላላሽ ተማሪዎችን እንዲያስተናግድ ተደርጎ ነበር የተከፈተው። ክቡር ዶ/ር አባ ወልደማሪያም ካሕሳይ ኢሮብ ካፈራቻቸው ለኢሮብ ህዝብ አሳቢ ምሁራን መካከል አንዱ ስለነበሩ፣ ያኔ በአዳሪነት መማር ያለባቸው ወጣቶችን ሲመርጡ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መላው የኢሮብ አከባቢዎችን የነበራቸው ቦታ በሚፈቅደው መጠን ፍትሓዊ በሆነ መልኩ ለማዳረስ በመሞከር ነበር። በዛን ጊዜ በልደታ ለማሪያም ት/ቤት በአዳሪነት እንዲማሩ ዕድል ያገኙት ተማሪዎች ቁጥር በትክክል ለማስታወስ ባልችልም በግምት ከ20 የማንበልጥ የነበርን ይመስለኛል።

ከልደታ ለማሪያም ት/ቤት በተጨማሪ ካቶሊክ ቤተክርስትያን፣ ቤተክርስትያናትን በተለያዩ የኢሮብ አከባቢዎች ስታስፋፋ፣ ከቤተክርስትያናቱ ጎን ለጎን የአከባቢው ልጆች ፊደል ሊቆጥሩበት የምችሉ መለስተኛ ት/ቤቶችም በመክፈት የትምህርት ዕድልን በማስፋት ለመቀጠል ችላለች። ከነዚህ ከካቶሊክ ቤተክርስትያን ጋር ከተያያዙት መለስተኛ ትምህርትቤቶች ውጭ በመላው ኢሮብ እስከ 1966 ዓ.ም. ድረስ ከልደታ ለማርያም ት/ቤት በስተቀር በትምርት ሚኒስቴር እውቅና የተሰጠው ሌላ በአከባቢው አልነበረም።

በ1966 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ በመንግሥት አንድ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት በዓሊተና ከልደታ ለማሪያም ት/ቤት ጎን ተሰራ። ሆኖም የአፄ ኃይለስላሴ መንግስት ገና በ1967 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ በወታደራዊ ደርግ ተወግዶ፣ ወታደራዊ ደርግ ስልጣን ስለያዘና አከባቢው ደግሞ ለተለያዩ የደረግ ወታደራዊ አገዛዝን የሚቃወሙ ሃይሎች መናኸሪያ ስለነበረ እስከ 1983 ዓ.ም. ድረስ በአከባቢው ምንም አዲስ ት/ቤት አልተሰራም።

ከደርግ ውድቀት በኋላ ከ1983 ዓ.ም. ኢህአዴግ በትረ-ሥልጣኑን እንደያዘ፣ የትምህርት ጥራትን ነገር ሳናነሳ በአካባቢው በተለያዩ መንደሮች አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች በመንግስትና በካቶሊክ ቤተክርስትያን በስፋት ባጭር ጊዜ ውስጥ መስፋፋት ጀመሩ። ከተለያዩ ምንጮች ባገኘሁት መረጃ መሰረት ዛሬ በኢሮብ ወረዳ ወደ 9 በመንግስት፣ እንዲሁም ደግሞ 11 በካቶሊክ ቤተክርስትያን የተገነቡ፣ በድምሩ ወደ 20 የሚሆኑ አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተገንብተዋል። ከዚህ በተጨማሪም ወረዳዋ ዛሬ የሁለት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ባለቤት ናት። ስለሆነም ዛሬ በኢሮብ ወረዳ የት/ቤቶች እጥረት ጉዳይ ተሻሽሏል ለማለት ይቻላል።

<u>**ዛሬ እንደ አንገብጋቢ ችግር ሊነሳና አስቸኳይ መፍትሄ ሊፈለግለት የሚገባው ችግር፣ ት/ቤቶች በየመንደሩ ተገንብተው ልጆች ሩቅ ሳይጓዙ በየሰፈራቸው መማር እየቻሉ፣ ሁለት 2ኛ ደረጃ ትምህርትቤቶችም በወረዳው ተከፍተው እያሉ እጅግ በርካታ ቁጥር ያላቸው የኢሮብ ወጣቶች**</u>

***<u>ሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና አልፈው ከፍተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ያልቻሉበት ምክንያት ምንድን ነው የሚለው ይሆናል።</u>***

*ሁላችን በሚገባ እንደምናውቀው ዛሬ በርካታ ወጣቶች ለህይወታቸው በጣም አስጊ የሆነ መንገድ ሁሉ በመጠቀምም ጭምር አከባቢውን ለቀው እየተሰደዱ ነው። ለነዚህ ወጣቶች ስደት በርካታ ሌሎች ምክንያቶች ሊኖሩ ቢችሉም ወጣቶቹ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በተገቢ ደረጃ ተከታትለው በመጨረስ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመቀጠል የሚችሉበት ተገቢ ውጤት ለማምጣት አለመቻል አንዱ ምክንያት ነው። ስለዚህ የወጣቶቹን ስደትና አስተሳሰብ ለመቀየር ዛሬ በኢሮብ ወረዳ ሰፍኖ ያለውን የትምህርት ዝቅጠት ለመቀረፍ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ከመፍትሄዎቹ አንዱና ዋነኛው ነው። ስለሆነም ወደ መፍትሄ ፍለጋ ከማቅናታችን በፊት አስቀድመን ችግሮችን በትክክል ለይቶ አንጥሮ ለማውጣት በሚቻልበት ሁኔታ፣ መረጃ ያላቸው ወገኖቻችን መረጃዎችን እያቀረቡልን፣ ሁሉን በሚያካትት መልኩ ውይይት ቢደረግ የሚፈለገው መፍትሔ ላይ ለመድረስ ያስችለናል ብየ አምናለሁ። ዛሬ በኢሮብ ወረዳ ትምህርት ምን ያህል ዘቅጦ እንዳለ፣ በርካታ ወጣቶቻችን በአካል በኢሮብ እየኖሩ ህልማቸው ሁሉ ስለ ባዕድ ሀገር እንደሆነ አቶ ዚያደ ኃይሉ በጎሮን ፎረም ላይ ከሁለት ወራት በፊት በለጠፉት ቀጥሎ በሠፈረው አጭር መልእክት በግልጽ አሳይተውናል። ለዚህም አቶ ዚያደ ኃይሉ ምስጋና ይገባቸዋል።*

**"(Living in Alitiena, thinking of Israel)**

**Analyze this: For starters here is the report card on Irob education according to the Woreda chief: out of 300 students who sat for 10th grade exams only 39 merely passed. And out of those 39 who participated in preparatory (12th) exams only 7 passed with no particular flying colors. And only God knows how those 7 succeed in completing the university degree. Besides school drop rate is hovering between 30%-50% - …"**

*እኔ ይህን የአቶ ዚያደ ኃይሉ መልእክት ከተመለከትኩበት ዕለት ጀምሮ ሌላውን የኢሮብ ህዝብ ችግሮች ለጊዜው ወደጎን በመተው ትምህርትን በተመለከተ በተለይ ለምንድን ነው እጅግ በርካታ ልጆች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቀው ከፍተኛ ትምህርት ለመቀጥል የሚያስችል ውጤት ለማምጣት ያልቻሉት? የሚለውን ጥያቄ በማንሳት በቀጥታ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የተለያዩ ወገኖች ጋር ለመነጋገርና መረጃዎችን ለማሰባሰብ ሞክሪያለሁ። ከነዚህ ወገኖች ባገኘሁዋቸው መረጃዎች መሰረት ዛሬ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ለማለት በሚያስደፍር ደረጃ ቀጥለው የተቀመጡት ሶስት ዓበይት ችግሮች ወጣቶቻችን ትምህርታቸውን በሚገባ ተከታትለው የሚፈለገውን ውጤት እንዳያስመዘግቡ ከሌሎች ችግሮች ጋር ተዳምረው ሲታዩ በዋናነት ከሚታዩ እንቅፋት ውስጥ የሚመደቡ ናቸው የሚል እምነት አድሮብኛል።*

*እነሱም፣*

1. ***<u>አብዛኛዎቹ በአስተማሪነት የሚመደቡ አስተማሪዎች ከመምህራን ማሰልጠኛ (በለብ ለብ) አጭር ስልጠና የተመረቁ ብቃትና ልምድ አልባ መሆን፣ አንዳንድ አስተማሪዎች የአስተማሪነት ሙያና ሥነ-ምግባር የሚጎድላቸው መሆን፣ አብዛኛው አስተማሪዎች ከማስተማር ስራ ይልቅ ለአንድ ድርጅት የፖለቲካ ካድሬነት ስራ ቅድሚያ የሚሰጡ መሆን፣</u>***
2. ***<u>በየትምህርት ቤቱ መሟላት ያለባቸው የትምህረት መስጫ ቁሳቁሶች በጣም የተጓደሉ ወይም ደግሞ የሌሉ መሆናቸው፣</u>***

3. <u>ተማሪዎች ትህርታቸውን በተገቢ ደረጃ ለመከታተል እንዲችሉ መመገብ ያለባቸው ተገቢ ምግብ ዕጦት ምክንያት የሚሰጣቸውን ትምህርት በሙሉ አትኩሮት ለመከታተል አለመቻል ከችግሮቹ ግንባር ቀደምቶቹ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ።</u>

እናንተስ ቅድሚያ የምትሰጧቸው ችግሮች የተኞቹ ናቸው?

ውድ ወገኖች፣ የእንደ እኛ ዓይነት ብሄረሰብ ህልውና መቀጠል፣ በዋናነት ወጣቱ ትውልዳችን በትምህርት ታንጾ ፣ ማንነቱን በሚገባ አውቆና ጠብቆ እንዲያድግ በማድረግ ላይ የተንጠለጠለ ስለሆነ ይህ የትምህረት ዝቅጠት ጉዳይ ከምንም በላይ ሊያሳስበንና ሊያስጨንቀን ይገባል። ስለሆነም እንደዚህ ዓይነት ለብሄረሰባችን የወደፊት ህልውና ወሳኝ የሆነ የወጣቶቻችን በጥሩ ሁኔታ ተምረው እንዲያድጉ አለማድረግ ምን ዓይነት ጥፋት ሊያስከትል ይችላል የሚለው ጥያቄ ሲነሳ የተወሰኑ ግለሰቦች ወይም ቡድን ጉዳይ ብቻ ተደርጎ መተው ወይም ደግሞ እንደ አንድ ተራ ነገር ተመልክቶ በዝምታ ማለፍ ፈጽሞ ተገቢ አይደልም። ስለዚህ አሁንም ችግሮቹን ለይቶ ለማወቅ የሚደረገው ውይይት አንድንም ሰው ወደ ጎን ሳይገፋ በመካከላችን መቀጠል መቻል አለበት።

እኔ Irob Scholarship and Education Support Program (ISESP) በሚል ስም የተጀመረው እንቅስቃሴ አከብራለሁ፣ ሆነም ግን በኢሮብ ወረዳ ዛሬ ሰፍኖ ያለው የትምህርት ዝቅጠት አሁን ISESP ባቀደው የተወሰኑ በጣት የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ለመርዳት በሚደረግ እንቅስቃሴ ብቻ ፈጽሞ ሊፈታ አይችልም ባይ ነኝ። ስለሆነም በጋራ ተወያይተን ወደ ዘላቂና ሁሉ አቀፍ መፍትሔ ፍለጋ ማምራት ይኖርብናል። ISESP እንዳለ እየቀጠለ፣ የተሻለ አማራጭ ይዞ የሚቀርብ ካለም እየተደመጠ፣ ISESP አሁን ያቀደው ዕቅዱን መቀየር አስፈላጊ ነው የሚል ሃሳብ ካለም እየተደመጠ፣….ወዘተ ራእያችን በኢሮብ ትክክለኛ ትምህርት ማስፋፋት አድርገን እየተደማመጥን በጥልቀት ብንወያይበት የተሻለ ሁሉም አቀፍ ትክክለኛ ውጤት ላይ መድረስ እንችላለን ባይ ነኝ። ስለዚህ ትምህርትን በተመለከተ ያሉትን መሰረታዊ ችግሮቹን ለይተን ለማውጣት፣ ትምህርትን አስመልክቶ በተለያየ ስም የሚደረጉትን እንቅስቃሴዎች ወደ አንድ ለማምጣት ያለመ፣ የሰከነ፣ መደማመጥና መቻቻል የተሞላበት ውይይት በመካከላችን መቀጠል አለበት እላለሁ።

የኢሮብ ችግር በኢሮቦች የጋራ ርብርብ ይፈታል!!!

በክፍል አራት እስከምንገናኝ ለሁላችሁም መልካሙን ሁሉ እመኛለሁ።

መልካም ውይይት፣

ከኔጋር ለሚደረግ ግኑኝንት፣ beyene54@yahoo.com መጠቀም ትችላላችሁ።